# ትግላችን

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

ወርሃዊ መፅሄት

የኢት ዮጵያ ወዝአደርና አርሶአደር እንዲሁም
ሌሎች የተጨቆናችሁ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ
ተደራጁ !!
ተደራጅታችሁም ለንዑስ ከበርቴው ጊዜያዊ መን
ግስት ሳይሆን ለራሳችሁ መንግስት ታገሉ!!

c/o P. O. BOX 3198
10364 Stockholm 3
SWEDEN

ቁጥር፡ 1

ጥቅምት 1967

## ማውጫ

I ርዕሰ አንቀጽ ........................ከገጽ2 እስከ 5

II በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
አመታዊ 14ኛ ጠ/ጉባዔ የፖለቲካ ውሳኔ ....ከገጽ6 .. 9

III የውሳኔዎችን ታሪካዊ ትርጉም ............ከገጽ10.. 32

1. በየካቲቱ እንቅስቃሴ የንዑስ ከበርቴውና
የወዝአደሩ ሚና ..................ከገጽ12.. 22

2. የጊዜያዊ መንግስት ጥያቄ ...........ከገጽ22.. 28

3. አንድ ፓርቲ ወይስ ብዙ ፓርቲዎች .....ከገጽ28.. 32

IV ስለኃይለ ሥላሴ መውደቅ ከአሲተማ የሥራ
አስኪያጅ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ .........ከገጽ33.. 35

V የኃይለ ሥላሴ መውደቅ ..................ከገጽ36.. 63

1. የኃ.ሥ. መውደቅ የየካቲት እንቅስቃሴ
አንድ ውጤት ነው።..................ከገጽ39.. 42

2. የኃ.ሥ. መውደቅ የኢት.ህዝቦች ይደገፋሉ.ከገጽ42 ..45

3. ኃ.ሥ. ስለወደቀ እና የምንታገለለት ሬቮሉ-
ሽን ተደረገ ማለት አይደለም..........ከገጽ45.. 47

4. የኃ. ሥ. መውደቅና ተግባራችን ......ከገጽ47.. 63

VI የዓለም ዐቀፍ መዝሙር ................ ገጽ64

VII ዋጋው አያሌ ነህ ሙሉተ ግጥም ...........ከገጽ65.. 66

## ርዕሰ አንቀጽ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 14ኛ ጠ/ጉባዔ በበርሊን ከተማ ከኦገስት 13 እስከ 19 ተደርጎ ነበር ይህ ጉባዔ የተካሄደው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ጭቆና አንገፍግፎት በገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ላይ በነበረበት ወቅት ነው::ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በተጨቆነው ሕዝብ ወገን በመሰለፍ ከፊውዳሊዝም ከኢምፔሪያሊዝምና ከኃይለ ሥላሴ የፋሺስት አገዛዝ ጋር የማይቋርጥ ትግሎች ያካሄደው ማህበራችን ለጉባዔው የሰጠው የመወያያ አርእስት 'ጊዜያዊ የኢትዮጵያ ሁኔታና ተግባሮቻችን' የሚል ነበር::

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ብቻ ያነሱዋቸው የነበሩት ጥያቄዎች፣ ይዋጉላቸው የነበሩት ዓላማዎች ዛሬ የራሱ የሕዝቡ ሆነው፣ ሕዝቡም በነዚሁ ጥያቄዎችና መሪ ቃሎች ሥር ተሰልፎና ታግሎ ብዙ የማይናቁ ድሎች ተጎናጽፎአል::

ተማሪ ያነሳቸው የነበሩ መሪ ቃሎችና ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አሁን የሕዝቡ በመሆናቸውና ከየካቲት ወዲህ የሚደረጉት ትግሎች ያስገኙት ድል ምክንያት የተማሪው የከንግዲህ ተግባር እንደ ድሮ አጠቃላይ ጥያቄዎችን በማንሳት ሳይሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል በከፍተኛ ደረጃ ቀጥሎ እንዴት ወደመጨረሻው ግብ እንደሚደርስ መንገዱ መፈለግና ትግሉ ለሚያነሳቸው ተጨባጭ ጥያቄዎች ተጨባጭ መልስ ወደመስጠትና ተጨባጭ ሥራዎችን ወደ መስራት እንዲሸጋገር ያደርጉታል::



የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ጀመረ እንጂ ገና አላከተመም::እስካሁን የተደረጉት ትግሎች፣ የተገኙትም አንዳንድ ድሎች፣በረዥሙ የነጻነት ትግል ጉዳና አዳዲስ ምእራፍ ከፋቾች እንጂ የመጨረሻዎች ትግሎች፣ የመጨረሻዎቹድሎች አይደሉም::

ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ሳይደመሰሱ፣በነሱም መቃብር ላይ በወዝአደሩና በገበሬው አንድነት ላይ የተመሠረተ ሌሎችንም ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች የሚጠቀልል ሕዝባዊ መንግስት ሳይመሠረት፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመጨረሻውን ድል ሊጎናፀፉ አይችሉም::አዲሲቷንም ኢትዮጵያ መገንባት እንዲሁ አይቻልም::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከንግዲህ ለራሳቸው ማቅረብ ያለባቸው ጥያቄ፣ መልሱን መሻት የሚገባቸው ጥያቄ፣ እዚህ የደረሰው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እንዴት በከፍተኛ ደረጃ ወደፊት መቀጠል አለበት? በተገኙትስ ድሎች ተጠቅሞ ለመጨረሻው ድል የሚያደርሰውን ዝግጅት እንዴት ሊያደርግ ይቻላል?የሚሉት ናቸው::

በጠቃላይ አነጋገር፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል አሁን ያለውን የተበታተነ መልኩን ቀይሮ፣ ተደራጅቶና ካሁኑ የበለጠ የፖለቲካ ንቃት ኖሮት ትግሉን ቢቀጥል ብቻ ከመጨረሻው ግብ ሊደርስ እንደሚችል ለተራማጆች ሁሉ ግልጽ መሆን አለበት::

ያንዱ ሕዝብ ትግል ሺህ ጊዜ አብዮታዊ ቢሆን፣ ሳይደራጅ የመጨረሻውን ድል ሊያገኝ አይችልምና የኢትዮጵያ ተማሪዎች

ሕዝቡ እንዲደራጅ ለመርዳት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ታጥቀው መነሳት አለባቸው። 'ተማሪና ምሁር ከሕዝቡ ጋር ተዋሀዱ፣ከነሱም ተማር ፣ መልሰህም አስተምራቸው፣ አብረህም በመሰለፍ አዲሲቱን ኢትዮጵያ መስርት።' የሚለው የማህበራችን መሪ ቃል በመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን በሥራ ላይ መዋል አለበት።

ከዚህም ጋር በማያያዝ፣በሕዝቡ ትግል የተገኙ ድሎች በአድሃሪዎች እንዳይነጠቁ፣ የሕዝቡን የወደፊት ትግል ለማቆም የሚፈልጉ ሪፎርሚስቶች ለሕዝቡ ማታለያ እንዳይጠቀሙበት ነቅቶ መጠበቅና መታገል ከጊዜያዊ ዋና ተግባሮቻችን አንዱ ነው።

በመጨረሻም፣ከለአብዮታዊ ቲዎሪ አብዮታዊ ትግል የለምና የተማሪ ማህበራትም ሆኑ አበሳት የፓለቲካ ንቃታቸውን ከፍ ለማድረግና ከሌሎች ፀረ—ፊውዳሊስት ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግሎች ታሪክ ትምህርት ለመቅሰም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

ይህ ታሪካዊ ትግል ወደዱል ጉዳና ሲያመራ የሚችለው ቢደራጅና በከፍተኛ ንቃት ወደፊት ቢራመድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣ጊዜያዊ ተግባሮቻችን ሕዝቡ እንዲደራጅ መርዳት፣የተገኙት ድሎች በአድሃሪዎች እንዳይነጠቁ ነገር ግን ገና ለመሰረታዊ ለውጥ መታገል ያለብትን ሕዝብ እንዳያታልሉት ነቅቶ መጠበቅና መታገል መሆኑን ከተገነዘብንና በዚህም አቀጣጫ የሚቻለንን ከሰራን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለነጻነታቸው በሚያደርጉት ረጅም ትግል በሁኑ ወቅት ድርሻችንንና ያለብንን ሃላፊነት በሚገባ ተረዳን ማለት ነው።



ነገር ግን 'ይህንን ሃላፊነታችንን ለመቀበል ባይስካልን ቀርቶ ወደእውነተኛ ነጻነት የሚወስደውን የተደራጀ የትግል ጉዳና እንዲይዝ ሳናገዘው ቀርተን ሕዝባችን የተበታተነ ትግሉን ቢቀጥል፣ በዚህም የተነሳ በዘመናት ጭቆና ገንፍሎ በብዙ ሰማዕታት ደምና ስቃይ እዚህ የደረሰው ትግል መሰብሰብ አቀቶት በተደፈቹ ፀረ—ሕዝብ ሃይሎች ቢገታ፣የተገኙትን ድሎች ምንነት ሳናስረዳው ቀርተን ሕዝቡ ዘረ የትግሉን አመራር በያዙት የንዑስ ከበርቴ ሪፎርሚስቶች ቢደለል፣ በታሪክ ወንበር ፊት የሚያስጠይቀን ይሆናል።

ስለዚህ ለዚህ ሁሉ ታሪካዊ ሃላፊነት ብቁ እንሆን ዘንድ ድርጅታዊ አንድነታችንን ጠብቀን ትግላችንን እንቀጥል።

ድሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ነው

'ትግላችን'

## በ14ኛው የአውሮፓ ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በአብዛኛዎች ተደግፎ ያለፈ የፖለቲካ ውሳኔ

1ኛ፡— የየካቲት አንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወደር የሌለው ሰፊ የሕዝቦች አንቅስቃሴ ነው። በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉት የመደብ ፣ የብሔር ፣ የሃይማኖት ፣ የጾታ ቅራኔዎች በይፋ እንዲገለጹ ያደረገ አንቅስቃሴ ነው። በጉልተኛና በጪሰኛው መካከል ፣ በከበርቴውና በወዝ አደሩ መካከል ፣ በጨቋኝና በተጨቋኝ ብሔረ—ሰቦች ፣ ሃይማኖቶችና ጾታዎች መካከል ፣ በጠቅላላው በሥርዐቱ በኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ሕዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች በይፋ እንዲወጡ ያደረገ አንቅስቃሴ ነው። ከመቼውም ይበልጥ ገዢ መደቦች ባንዱ በኩል ተነጥለው ፣ ተጨቋኝ መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች በሌላው በኩል ተሰልፈው እንዲታዩ አድርጓል። ይህ አንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍ ያለ ቦታን ይይዛል።

2ኛ፡— የዚህ አንቅስቃሴ ጊዜያዊና መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። መሠረታዊ ምክንያቶች እየጠመሩ የመጡት የጉልተኛው ሥርዐትና የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ ናቸው። ጊዜያዊ ምክንያቶች ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የደረሰው ረሃብ ፣ የጠቅላላው የኢምፔሪያሊስት ዓለም የኢኮኖሚ ችግር—ክሪዝ— ፣ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ላይ የተጫነው የኑሮ ዋጋ መወደድ ናቸው።



3ኛ፡— በየካቲቱ አንቅስቃሴ የተሳተፉት የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ መደቦች የወዛደሩ ፣ የትንሽ ከበርቴውና የገበሬው ሲሆኑ በጠቅላላው አንቅስቃሴውን የጀመረውና የመራው የትንሽ ከበርቴው መደብ ነው። የትግሉ ዘዴ ሥራ ማቆም ፣ ሰላማዊ ሰልፍና ገበሬውን በሚመለከተው በኩል አመፅ ነበር። ከየካቲት 28 እስከ መጋቢት ሁለት የተደረገው ጠቅላላ ሥራ ማቆምና የወዝአደሩ መደብ በታላቅ ዲሲፕሊን እንደ አንድ ሰው ሆኖ መውጣት በአገሪቷ የትግል ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ነበር። የቀረቡት ጥያቄዎች ‘መሬት ላራሹ ፣ የመናገርና የመጻፍ የመሰብሰብ ነጻነቶች ፣ የብሔረሰቦች ፣ የሃይማኖቶች ፣ የጾታዎች እኩልነት’ና የመሳሰሉ የዲሞክራሲያዊ ነጻነቶች ጥያቄዎች ነበሩ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የየካቲት አንቅስቃሴ የቡርዧ ዲሞክራሲ ሬቮሉሽን መልኮች የያዘ ሰፊ ሬቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ ነው።

4ኛ፡— የየካቲት አንቅስቃሴ የአክሊሉ— አካለወርቅ—ማሞ ታደሰን የቢሮ ከበርቴዎች መንግሥት ጥሎአል። የትላልቅ ባላባቶች ዋናዋና ወኪሎች ከመንግሥት ሥልጣን አስወግዶአል። ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ፈጥሮአል። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትግሉ ብዙ ትምህርቶችን እንዲቀስም አድርጓል። በዚህም ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የወደፊት ትግል ይበልጥ የሚያመች አዲስ ምእራፍ ከፍቷል። ፍፁም የማይናቁ ድሎችን አስገኝቷል።

የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ዋና ዓላማ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በመደምሰስ በወዝአደሩ መሪነት በርቱና በአርሶ አደሩ አንድነት ላይ የተመሰረተ ሌሎችን ፀረ—ፊውዳሊስትና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በሚጠቀልል ያንድነት ግንባር አማካይነት የፓለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ ነው::ይህም በወዝአደሩ የሚመራ ያንድነት ግንባር ከቀደሞው ስርዐት የተላለፈውን መንግስት ይደመስስና በቦታው እውነተኛውን ሕዝባዊ መንግስት ይተካል::ይህ እኛ የምንታገልለት ሕዝባዊ መንግስት ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም መውደም ቀደም፣ ከሕዝቡ የተደራጀ የጦር ትግል በፊት ሊመጣ እንደማይችል ቋሚ እምነታችን ነው::

ዛሬ ሁሉም በየፊናው 'ሕዝባዊ መንግስት' የሚልበት ወቅት ነው::ስለዚህ ሕዝባዊ መንግስት በቋራጭ የማይገኝ በሕዝቡ በራሱ የተደራጀ የፖለቲካና የጦር ትግል በኋላ ብቻ ሊመጣ እንደሚችል፣ ከሕዝቡ የተደራጀ የጦር ትግል በፊት ከኢምፔሪያሊዝምና ከፊውዳሊዝም መውደም ቀደም የሚመሰረት መንግስት እራሱን ሺህ ጊዜ 'ሕዝባዊ' ቢል የወዝአደሩንና የአርሶአደሩን ጥቅምና መብት ሊያስጠብቅ የሚቆም እንዳልሆነ ደግመን ደጋግመን መግለጽ አለብን::

እኛ የምንታገልለት ሕዝባዊ መንግስት ምን ዓይነት እንደሆነና እንዴትስ ሊፈጠር እንደሚችል ከዚህ በላይ በጭሩ ገልፀናል:: ሕዝባዊ ለማስመሰል 'ከሕዝባዊ ድርጅቶች የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም' ስለሚባለው ያለንን አቋም ከዚህ በታች በጭሩ እናስፍራለን::



አንዴ አብዮታዊ ትግል እየተካሄደ ባለ የመንግስትን ሥልጣን ማንም ብቻውን ሊይዝ የማይችልበት ሁኔታ ሊደረስ ይቻላል:: በዚህም ጊዜ ወዝአደሩ ወይንም በወዝአደሩ የሚመራው ያንድነት ግንባር ሌሎች ኃይሎች ጭምር የሚሳተፉበት 'ጊዜያዊ መንግስት ይቋቋም' የሚል መሪ ቃል ያወጣል::እንዲህ ዓይነቱ ጊዜያዊ መንግስትም ሊመሰረት ይችላል::አብዮቱን የሚያካሄደውን ሠርቶ አደር ሕዝብ የሚመራው ድርጅት ይህንን መሪ ቃል ሲያወጣ፣ በሚቋቋመውም ጊዜያዊ መንግስት ውስጥ ሲካፈል በተደራጀው የጦር ኃይሉና በሚኖረው የድርጅት ነጻነት በመተማመን ነው::ማለትም የተደራጀ የጦር ኃይል ሳይኖረውና ድርጅታዊ ነጻነት ሳያገኝ የሠርቶ አደሩ ድርጅት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም አይልም:: በንዲህ ዓይነቱም ጊዜያዊ መንግስት ለመካፈል አይሞክርም::በሌላ አነጋገር እውነተኛ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ከሕዝቡ የተደራጀ የጦር ሃይልና ከኢምፔሪያሊዝምና ከፊውዳሊዝም መውደም ወይም መዳከም ቀደም ሊመጣ በፍፁም አይችልም::

'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም' የሚለውን መሪ ቃል አብዮታውያን ያቀረቡበትን ሁኔታ ስናይ ከላይ ያልነውን ሀቅ ያረጋግጣል ::ሌኒን 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም'በሚል መሪ ቃል ስር የሩሲያን ወዝአደር መርቶ ነበር::ይህም መንግስት የገበሬውና የወዝአደሩ ዲክታተርነት እንደሚሆንና ከሕዝባዊ የጦር ሃይል ጋር በአንድ ሰንጢም ላይ እንደሚገኙ 'ዘውዱና አንበሳ' (- two si
f the same coin) እንደሆኑ ያስተምረናል::በቻይናም እንዲሁ በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነት የተደራጀ የጦር ትግል ያካሄዱ የነበረው ድርጅት ጊዜያዊ የኮሊሽን ይቋቋም የሚል መሪ ቃል ነበረው::

ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ሲገነባ ብቻ ነው፡፡

እንደማንኛውም ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብም ወደዚሁ ቋሚ ነጻነቱ ለሚያደርገው ትግል፣ ያለው መተማመኛ፣ የራሱ የፖለቲካ ንቃት፣ የራሱ የተደራጀ ትግልና የራሱ ድል ብቻ ነው፡፡ ቋሚ ነጻነቱን 'እንደመና' ከሰማይ አያገኘውም፡፡ ወይንም ደግሞ በሞግዚት ተጠብቆ አይጎናፀፈውም፡፡

ስለሆነም በፊትም ሆነ አሁን ለሰፊው ሕዝብ ደጀን ሆኖ የሚቆመው የሰፊው ሕዝብ መሣሪያ መደራጀቱ ብቻ ነው፡፡

ከዛሬ በፊት ደጋግመን እንዳሰማነው ለዘመናት የተበደለውና የተጠቆነው የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ብዙ ናቸው፡፡— መሬት ላራሹ ይሁን

— የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ይሰ ምንም ገደብ ይከበሩ
— የወዝአደሩ መብቶች ይከበሩ
— ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት ይከበር
— የሃይማኖቶችና የጾታ እኩልነት ይኑር
— ብሔራዊ መብታችንን የደፈሩት ኢምፔሪያሊስቶች ከአገራችን ገጽ ይጥፉ ይሳል፣ ለዚህም ይታገባል፡፡

እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ከሥራ ላይ እንዲውሉ፣ የጭቆኑ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ያለ እንዳች ገደብ እንዲከበሩ መታገልና፣ እስከዛሬም በብዙ መስዋዕትነት የተገኙት



ድሎች በአድሃሪ ሃይሎች ተመልሰው እንዳይነጠቁ ነቅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

የዘውዱ አገዛዝ ይውደቅ
ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ
ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ይኑር
ድሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

## በፈረንሳይ ቅርንጫፍ ማህበር የተዘጋጀ

### ዓሰም ዓቀፍ

ተነሱ እናንት የረሃብ እስረኞች፣
ፍትህን ስሟት ትጠሃለች፣
ባህር ውቂያኖስ ተራራ፣
አቋርጣ ስትጣራ።
ባለፈው መታሰር ይበቃ፣
ሳብ አደር በቃ ንቃ።
ያሰም ገጽቀ ብሩህ ይሆን፣
ኢመንት ነን፣እልፍ እንሁን።

<u>አዝማች</u> ዓሰም ዓቀፍ ትገሳችን ዛሬ ነው ታገሉ
ነገማ ብርሃን ነው ለሰው ልጅ በሙሉ ( 2 ጊዜ )

ሥርዐትና ወጉ ገፊኛ፣
አዳይ ሕገ፣ ሌብ ዳኛ
በቃ ይውደሙ ይደምሰሱ፣
ሳዲሱ ቀን ተነሱ።
ፍቀር በሳም እንዲሰፋፋ፣
ሳዲስ ዓሰም በዲስ ተሰሩ
ሳብ አደር ተነስ ተሰለፍ
ዳር እስከ ዳር ዓሰም ዓቀፍ

አዝማች፡ ( በዱጋሚ ሁለት ጊዜ )

## ሲሁን በማዘሪያ

[illegible]
ነገገገር ገገቷ
ከኒን፣ ሥሰትን፣ ብበ፣ማይሙራበው ጫቷ።
ገናዉ ጊዜ አራቶ ባገመሬው አበፍቷል
ቤፍ፣ በንዴዉ፣ማሸሳውን፣ባ ንስሎም መቀቷል
ቷርቆና በበሶም ተበሬይቶ ገበቷል
የሁለቸንም ሀይን እንጀራ ነው ያየ
ገን ዘበበበሉ ምነው ፀገን ለየ?
ብረት ምጪዱ ጥደን ቶሎ እንጀራ እናወጣ
የተራበው አበሸ በልቶ ውሃ እንዲጠጣ
ሲሁን በማዘሪያ ቀዱተን በዚህ ሁሳ
ሳሕዝቡ እናዱለው የእኛም ወሰፋት ይሙላ
የሰም እንደወጉ በምጪቀ በስሉ
ባይዝ፣ ባይነኮር ይበሳ ቀስ በሉ
በሚል ስንጣሳ ርሃብ ጉኑ ሰፋ
ገበቸን አንዱ ባሳ እንጀራ ጥፍጠፋ
የትም በምን ይበስል ሙች ይሆናል ጨጣ
እንጀራው ተጋገሮ ሲበሳ ከመጣ
ሲሁን በዋርማ ባስፈለገ እንጠጣ
በቻ ተመገደ አርሃብ ካገር ይውጣ

ከዚያ ወዲያ መምረጥ ወግ ነው ያስተቀለ
ለነፋስ አንመቺ ተጣልተን በሌላ
እንደባቢሎን ግንብ አይፈርስም ሸንጎአችን
አንድ ነው ቋንቋችን አንድ ነው ግባችን
ነፃ እንጀራ ለሕዝብ ነፃ ለራሰችን
የመገባበት አርሃብ ወጡ ከጉያችን
ባንድ እንጀራ እንጋገር ሰይበርድ ምጣዳችን

—— ፣ ፣ ——

አያልነህ ሙሰቶ
9-11-73
<u>ሞስኮ</u>

አንብቡ፤ አስነብቡ ፤ተቹ ፤ተከራከሩበት

ዋጋው ፡ 1 50 ብ.